የአውሮፓ ኅብረት እና የአሜሪካ አምባሳደሮች መግለጫ

የኢትዮጵያና የሕዝቧ የረጅም ጊዜ የግንባታ አጋር እንደመሆናቸው የአሜሪካ መንግሥትና የአውሮፓ ኅብረት፣ ከሰፊው ዓለም አቀፋዊ ማኅበረሰብ ጋር በቅርበት ተባብረው በመሥራት፣ ከምርጫው በኋላ በተከሰተው ቀውስ መፍትሔ ለማስገኘት በተቃዋሚዎችና በመንግሥት መካከል ፖለቲካዊ ውይይት እንዲደረግ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል፡፡

ሁሉም የፖለቲካ ፖርቲዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨማሪ ወይም ቀጣይ ሁከት ከመፍጠር እንዲታቀቡና የሕግ ሥርዓትንና ሕገ መንግሥቱን እንዲያከብሩ አስቸኳይ ጥሪ እናደርጋለን፡፡ የፖለቲካ ዓላማዎቻቸውን በሰላማዊ ፖርላማዊ እና በዲሞክራሲያዊ የከተማው ምክር ቤት አማካይነት ሊፈልጉና ሊያሟሉ ይገባል፡፡

አንዳንድ ወይም ጥቂት የተቃዎሚ ፖርቲ አባላት በፖርላማ መቀመጫቸውን ቢይዙም፣ ኢህአዲግና ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እስከ አሁን ድረስ በውይይት ለመፍታት አለመቻላቸው ለረብሻው መነሻ በመሆኑ፣ በፖርላማውና በዲሞክራሲ ግንባታው ሂደት ተአማኒነት ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ረብሻው በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍአዊ ገጽታም ላይ ጉዳት አስከትሏል፡፡

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፖርቲ መሪዎችና አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ አባላት በቁጥጥር ሥር መዋልም ከፍተኛ ሥጋት ያሳደረብን መሆኑንም መግለጽ አለብን፡፡

ሁከተኛነት ከቁጥጥር በላይ ንሮ የሚያሳዝኑ ሁኔታዎችን አስከትሏል ሞትና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ቤተሰቦች ልባዊ ሀዘኔታችን ስንገልጽ፣ ከጸጥታ አስከባሪ ኃይሎችም ሆነ ወይም ትዕይንተ ሕዝብ ከሚያደርጉ ወገኖች የሚሰነዘረውን በኃይል መጠቀምና ረብሻን በሙሉ በማውገዝ ነው፡፡ ሕጻናት በረብሻ ውስጥ አለመኖራቸውንና መብታቸውን መከበሩንም ሁሉም ወገኖች ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

ሰሞኑን የደረሱት አሳዛኝ ክስተቶች መጠራጠር፣ እንደዚሁም የፖለቲካና ማኅበራዊ ክፍፍል በበለጠ ሥር እንዲሰዱ አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሰላማዊና ፍትሐዊ መንገድ ከፊቱ ያለ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልገው አጥብቀን እናምናለን ለዚህም ዓላማ መንግሥት በዲሞክራሲ ግንባታው ሂደት ሰላምንና መተማመን መልሶ እንዲያሰፍን እናበረታታለን፡፡ ይህንንም ለማድረግ የሚችለው የሕግን የበላይነትና /DUE PROCESS/ የሰብዓዊ መብቶችን መከበር መንግሥት በተቀበላቸው ግዴታዎችና በዓለምአቀፋዊ አሠራርም ተግባራዊ የሚሆኑት በግብር መዋላቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡

ስለዚህም መንግሥት፣ እስከሚመለከተውም ድረስ ተቃዋሚው ወገን፣ ከዚህ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንዲወስዱ እንጠይቃለን፡፡

- ሕይወት በሚቀጥፍ ኃይልና መሣሪያ መጠቀም፣ በዘፈቀደ ፍተሻ፣ ጅምላ ድብደባና በብዛት እያፈሱ በቁጥጥር ሥር ማዋል አሁኑኑ በአስቸኳይ እንዲቆም፣
- የፖለቲካ ታጋቾች በሙሉ እንዲፈቱ፣
- በቅርብ ጊዜ በተደረጉ ተቃውሞዎች ምክንያት የታሠሩ ግለሰቦች ሁኔታ በአፋጣኝ እየተገመገመ አግባብነቱ ተጣርቶ ቶሎ እንዲፈቱ፣

- ባልታገቱት የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መሪዎችና አባላት ላይ የተጣለባቸው ገደብ አሁኑኑ እንዲነሳ፣
- የታሠሩትን የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ፣ የሲቪክ ማኅበረሰብና የመገናኛ ብዙሐን መሪዎች ቤተሰቦቻቸው፣ ጠበቆቻቸው፣ ዓለምአቀፍአዊ የቀይ መስቀል ኮሚቴና/ ወይም አግባብ ያለው ሌላ የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ተወካይ እንዲገናኙ ዋቸው፣ እንደዚሁም የመድኃኒት የምግብና የሌሎችም ለሰው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አቅርቦት አሁኑኑ እንዲፈቀድ፣
- የታጋቾች ስምና የሚገኙበትም ሥፍራ ለየቤተሰቦቻቸው እንዲገለጽና መገናኘትና አስፈላጊ ነገሮችንም ማቅረብ እንዲፈቀድላቸው
- ሰሞኑን በተከሰተው ሁኔታና ባለፈው ሰኔም በደረሰው ሁከት የደረሰው ሞትና መቁሰል በገለልተኛ ወገን እንዲመረመር፣
- በፖርላማ የተወከሉ የፖለቲካ ፖርቲዎች በሙሉ ትክክለኛ በሆነ ተወካይነት መሠረት በሥራው መሳተፍ እንዲችሉ፣ የፖርላማውን ደንቦችና አሠራር ገምግሞ ማሻሻል እንዲደረግ፣
- የተመዛዘነ እና ኃላፊነት ያለው መረጃ ፍሰት ለሕዝብ መድረሱን ለማረጋገጥ፣ የግል መገናኛ ብዙሐን /ጋዜጦች/ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ መፍቀድና ሙያዊ ሥነ ምግባርን እንዲያከብሩ ማድረግ፣
- ከፖርላማዊ ተቃዋሚ ጋር በመመካከር ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን መሾም::

ተቃዋሚዎችን በሚመለከት፣ ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ በጣም አሳሳቢ በሆነ ወቅት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሁከት ከሚያነሳሳ በሰውና በሕዝብ ንብረት ላይ ጉዳትና ጥፋት ከሚያደርስ ማናቸውም እርምጃ እንዲቆጠቡና ሌሎችም ይህን ከማድረግ እንዲቆጠቡ እንዲመክሩ እንጠይቃቸዋለን::

የእርቅ ማውረድ መንፈሰን ለማራመድ በማሰብ፣ የአውሮፖ ኅበረትና የአሜሪካ አምባሳደሮች ሰላምን የሚያስገኝና ጠንካራ ዲሞክራሲያዊት ሀገርን መገንባት የሚያስችል የፖለቲካ ውይይት መደራደር እንደገና እንዲጀመር ያሳስባሉ::